# የጓድ ኣለሙ በፍቃዱ
# ኣጭር የሂወት ታሪክ



## ከ 1954 - 2015 (እ.ኤ.አ)

" ኣምላኬ ሆይ ኣንተ ከኔ ጋር ነህ

እና ሞትንም ሆነ ክፉን ሁሉ ኣልፈራም

በትር እና ምርኩዝህ ያጽናኑኛልና "

# የ አቶ አለሙ በፈቃዱ አጭር የ ህይወት ታሪክ

አቶ አለሙ በፍቃዱ ከአባቱ አቶ ፈቃደ አለሙ እና ከእናቱ ወ/ሮ አልጋነሽ ተሾመ 1954ዓ.ም. በወሎ አስተዳደር በቦረና አውራጃ ተወለደ። አቅሙ ለትምህርት ሲደርስ በመካነ ሰላም ት/ቤት በመግባት የአንደኛ እና ሁለተኛ መለስተኛ ት/ቤት ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት  አጠናቆ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ደሴ በመሄድ የወ/ሮ ስህን ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት ተቀላቀለ። ከዚያም ባስገኘው ከፍተኛ ውጤት ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ጀነራል ዊንጌት የትምህርት ተቋም ገባ 1966 ዓ/ም ኢትዮጵያ ውስጥ በፈነዳው አብዮት በጊዜው የነበረውን የተማሪዎችን እንቅስቃሴ ተቀላቀለ ሁላችንም እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ በወቅቱ የነበረበት የድህንነት እና የህግ መዛባት የሁሉም ህብረተሰብ አንገብጋቢ እና አሳሳቢ ጉዳይ ስለ ነበረ እና ለዚህም መፍትሄ ለመስጠት የሚችል ህዝብ የመረጠው አካል ባለመኖሩ በወቅቱ ስልጣን የያዘው መንግስትም ይህን አንገብጋቢ ጉዳይ መፍትሄ ለመስጠት የማይ ፈልግ እና ብቁም ባለመሆኑ የኢትዮጵያ ወጣቶች አማራጭ ብለው ወደ ጀመሩት የትጥቅ ትግል ለመቀላቀል በ1968 ዓ.ም. ከስድስት አብሮ አደጎቹ ጋር በረሃ በመግባት አሲምባ ላይ ከመሸጉ ወንድሞቹ እና እህቶቹ ጋር ተሰለፈ።

ከዚያም ትግሉን መቀጠል በማይችልበት ሁኔታ በመድረሱ በጅቡቲ አድርጎ 1982 ዓ.ም. አሜሪካ ገባ ። ኑሮውንም በአርሊንግተን ካውንቲ በመመስረት ከ ወ/ሮ ጌጤ ጃተማ ጋርም ተጋብቶ ኢትዮጵያን አብርሃምን እና ዳንኤልን ወለደ አቶ አለሙ በዚህ ወቅት ሁለት ስራ እየሰራ በኖቫ ኮሌጅ ትምህርቱን ተከታትሎ ተመረቀ ሌት ከቀን ያለ እረፍትም በኢትዮጵያ ህዝብ ጉዳይ ሰለቸኝ ሳይል የዜግነት ድርሻዉን ሲያበረክት የኖረ ዜጋና ትጉህ ሰራተኛ የቤተሰብ መሪ ሆኖ ቆይቶዋል

ከአቶ አለሙ ምኞቶቹም ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያ ሃገሬ አንድ ቀን ያለ ምንም ጥርጥር በጀግኖቻችን ነጻ ትወጣለች ቢሄድም እንኳን አርማየን ተተኪው ትውልድ ተረክቦ ረጅሙን የትግል ጉዞ በወኔ ይጓዛል የሚል ጽኑ እምነት ነበረው

አቶ አለሙ 2014 ዓ.ም. ጀምሮ በሰውነቱ ውስጥ በተፈጠረበት የካንሰር ህመም በህክምና ሲረዳ ከቆየ ቡሃላ ከመካከላችን በሞት ተለይትዋል።

" ሕያው ሆኖ የሚኖር ሞትንስ የማያይ ማነው?"
መዝ. ፹፰፡፵፰

## ምስጋና

አቶ አለሙ ታሞ በህክምና እርዳታ ላይ
እያለ በተደጋጋሚ እየተመላለሳችሁ
ለጠየቃቹሁን በፀሎታችሁም ላልተለያቹሁት
በቀብሩና በሀዘናችን ከጎናችን ሳትለዩ
ለረዳችሁን ላፅናናችሁን ሁሉ ለምንሰራቸው
በጎ ነገሮችን በምስክርነት የሚያየን
እግዚአቢሄር ለ መልካም ስራቹ በረድኤቱ
እንዳይለያችሁ እየተመኘን ልባዊ ምስጋናችንን
እናቀርባለን።

ቤተሰቡ በሙሉ